District of Columbia
Office of the State Superintendent of Education

ማጠቃለያ እና ምልከታ፡ ለልጆች ዕድገት መሰረተ ልማት ፈቃድ የመጨረሻ የሕግ አውጪ ክፍል

ዲሴምበር 2, 2016 ላይ፣ የመንግሥት የበላይ ባለሥልጣን ቢሮ በ D.C. Register (63 DCR 50) በኮሎምቢያ ግዛት በሙሉ የልጆችን ዕድገት መሰረተ ልማት ፈቃድ የሚገዛውን ሕጎችን በማሻሻል የመጨረሻውን የሕግ አውጪ ማስታወቂያን ያሳትማል። ሙሉው የመጨረሻው ሕግ አውጪ በhttp://bit.ly/2krnteR ላይ ይገኛል። የመንግሥት የበላይ ባለሥልጣን ቢሮ ለማድመቅ እና አንዳንድ የሚያስፈልጉ ቁልፍ ነገሮችን እና ለማጠቃለል እና የመጨረሻው የሕግ አውጪ ውስጥ የፍጻሜን ቀናት ለማስቀመጥ ይህን ማጠቃለያ እና ምልከታ ሰጥቷል። ሆኖም ግን፣ ይህ ማጠቃለያ እና ምልከታ በኮሎምቢያ ግዛት ከከተማ ጋር የተያይዙ ሕጎች ውስጥ በአንቀጽ 1 ርዕሰ 5ሀ ላይ የሚያፈልጉት ነገሮች እንደተቀመጠ ሁሉንም ሊይዝ አይችልም። ይህ ህትመት ሁሉንም ሕጎች ያካተተ ያይደል ሲሆን እንደ ኮሎምቢያ ግዛት ከከተሞች ጋር የተገናኘ ሕጎች በ5ሀ ምዕራፍ 1 ውስጥ ላይ የሚገኘው የመንግሥት ሕግ በተመሳሳይ ብርሃን አይወሰዱም።

የመጨረሻም የሕግ አውጪዎች ዓላማ:

የመጨረሻው የሕግ አውጪ ዓላማ በግዛቱ ውስጥ ፈቃድ በተሰጠው የልጆች እድገት መሰረተ ልማት እየቀረበ ያለው እንክብካቤ እና ትምህርት ደኅንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ብቻ ማረጋገጥ ሳይሆን፣ ነገር ግን በልጆች እንክብካቤ ላይ ጤናን፣ ደኅንነት፣ መልካም መሆን፣ እና አዎንታዊ ዕድገት እንዲኖር ለመጠበቅ ቢያንስ ሊያሟሉ የሚገቡ ነገሮችን በማቀመጥ የልጆቹን ጤናማ ዕድገት፣ የወፊቱ በትምህርት ላይ የሚያስመዘግቡት ውጤት እና ስኬት ይረዳል። በተጨማሪም፣ የመጨረሻው የሕግ አውጪ ቅርብ ጊዜ የተደረገውን ምርምር እና በልጆች ዕድገት ውስጥ ምርጥ ልምምድን ለማንጸባረቅ፣ የፌደራል የልጅ እንክብካቤ እና እድገት የእርዳታ ብሎክ አዋጅ 2014 (CCDBG Act)፣ ኖቨምቤር 19, 2014 (Pub. L. 113-186; 42 U.S.C. §§ 9858 et seq.) ከጸደቀው፣ እና በ45 C.F.R. ክፍል 98 እና 99 ሥር የተደነገጉት ሕጎች ሥር ተገዥ ለማድረግ፣ እና ከግዛቱ ጠቃሚ ከሆኑ ሕጎች እና የልጆች ዕድገት መሰረተ ልማት ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ደንቦች ጋር ለማስተባበር የግዛቱን የሕግ ማዋቅር ያሻሽላል።

መነሻ ሀሳብ:

የ CCDBG አዋጅ የግዛቱን ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ደረጃውን የጠበቀ የልጆች እንክብክቤን ለማሳደግ እና የተመጋቢዎችን ስምርት እና ለቤተሰቦች ትምህርት ብቃትን ለመስጠት የግዛቱ የልጆች ዕድገት መሰረተ ልማቶች ትርጉም ያለው ተሃድሶን የጠየቀውን በሕጋዊነት ሊያቀጡ የሚችሉ ለውጦችን ለማጽዳት ሰርቷል። የመጨረሻው የሕግ አውጪ ከግዛቱ የልጆች ዕድገት መሠረተ ልማቶች የደንቦች መዋቅር እና ከ CCDBG አዋጅ 2014 ጋር እና ከእርሱ ደንቦች፣ እንዲሁም ከ ለልጆቻችን እንክብካቤ ማድረግ ከሚለው ጋር ይሄዳል: ብሔራዊ የጤና እና የደኅንነት አፈጻጸም መመዘኛዎች፣ በከፍተኛ ደረጃ የ CCDBG አዋጅ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድረው፣ በልጅነት እንክብካቤ ስለመጠት እና የትምህርት መርኃግብሮች መምሪያ (ለልጆቻችን እንክብካቤ ማድረግ) የ መምሪያዎች። ለ CCDBG አዋጅ መልሶ ሥልጣን በሚሰጥበት ጊዜ፣ ይህ የመጨረሻው የሕግ አውጪ የቤተሰቦች አጋዥ፣ በኮሎምቢያ ግዛት ሁለቱንም ጥናማ የልጆች ዕድገትን አስተዋዋቂ፣ እና በግዛቱ ውስጥ በአጠቃላይ የልጆች እንክብካቤ ጥራትን በማሻሻል አካል እንዲሆን የታሰበ ነው።

የሕግ አውጪው ሂደት

በአሁኑ ጊዜ ያሉት አብዛኛው ሕጎች በምዕራፍ 3 ርዕስ 29 DCMR የመጨረሻው የተከለሱት በ2007 ነው።
በፈቃድ ሰጪ ህጎች ላይ የተደረጉት ማንኛውም ለውጦችን መረዳት በልጆች፣ በቤተሰቦች እና በግዛቱ ውስጥ የሚገኙት ንግዶች ቁጥር፣ የተሻሻለ የሕግ አውጪው የተነደፈው ማስታወቂያ በዲሴምበር 24, 2015 በ OSSE የተሰጠው እና ለሕዝብ ባለድርሻ አካላት አስተያየት ለማሰጠት በሴፕቴምበር 2016 ላይ የተሰጠው የሕግ አውጪው የተነደፈው ማስታወቂያ ላይ ትርጉም ያለው ተጽእኖ ይኖረዋል። OSSE አብዛኛው የሕዝብ ባለድርሻ አካላት በተነደፈው የሕግ አውጪ ፍላጎት ማሳየታቸውን እና ሕዝብ አስተያየት በሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየታቸውን በመስጠታቸው አድናቆቱን ይገልጻል። OSSE ሁሉንም የተሰጡትን አስተያየቶችን የመለከት እና ሙሉ በሙሉ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በዚያው መሰረት ለውጦችን አድርጓል። በአጠቃላይ፣ ባለድርሻ አካላት OSSEን ተነድፎ ቀደም ብለው የቀረበውን ሕግ እና የንድፍ ከለሳዎችን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲያጠለው እና እንዲያሻሽለው የሚያስችሉት ዋጋ ያላቸውን ዕይታዎችን እና አስተያየቶችን ይሰጣል። OSSE የአስተያየት ሰጪዎች በ CCDBG አዋጅ ውስጥ ካለው አቅራቦት ጋር፣ ከግዛቱ ሕጎች እና ደንቦች፣ ወይም ከልጆቻችን እንክብካቤ ጋር፣ ከብሔራዊ ጤና እና ለልጅነት ጊዜ እንክብካቤ ለድኅንነት ጥበቃ አፈጻጸም መምሪያዎች እና የትምህርት መርኃግብሮች ጋር የሚጋጩትን የሚጠይቅ ከሆነ በተቀበለው አስተያየት ላይ መሰረት በማድረግ በመጨረሻው ሕግ ላይ ማስተካከያዎችን አያደርግም። ለሕግ አውጪው ንድፍ ማስታወቂያ ሕዝብ አስተያየት በሚሰጥበት ጊዜ ለተሰበሰበው አስተያየቶች ምላሽ በመጨረሻው ሕግ አውጪ በመግቢያው ላይ ይገኛሉል።

የመጨረሻው የሕግ አውጪው ሕግ ከዲሴምበር 2, 2016 ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል። ሆኖም ግን፣ አንዳንድ አቅራቦቶች የአፈጻጸም የጊዜ ገደቦችን የሚከተሉትን አካቶ አዘግይቷል፡

- የጤና እና የደኅንነት አጠባበቅ ሥልጠና: የCCDBG አዋጅን መከተል፣ ሁሉም ፈቃድ የተሰጣቸው መሰረተ ልማቶች ከጤና እና ከደኅንነት አሁን ላሉት ሁሉም እና አዳዲስ የሠራተኞች አባልት ሴፕቴምቤር 30, 2017 ሥልጠና የሚያጸኑ መሆን አለባቸው። ፈቃድ ሰጪ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ፈቃድ በሚታደስበት ጊዜ ጤናው እና ደኅንነት ኮርሶች ያልተሟሉ ከሆነ የጉድለት ደብዳቤ የሚሰጡ ሲሆን ስለ አፈጻጸሙ ሴፕቴምቤር 30, 2017 ላይ ቁጥጥር ያደርጋሉ።
- የወንጀለኛ የኋላ ታሪኩን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ነገሮች: የ CCDBG አዋጅ መከተል፣ መሰረተ ልማቶች ከወንጀለኛው የኃላ ታሪክ ለመመርመር ከሚያስፈልጉ ነገሮችን አሁን ላሉት እና ለአዲስ ሠራተኛ አባላት በሙሉ ሴፕተምቤር 30, 2017 ላይ እንዲያዉ ይደረጋሉ።
- የሠራተኛው ብቃቶች: ለልጆች ዕድገት ማዕከል ዳሬክተሮች፣ አስተማሪዎች፣ እና የአስተማሪዎች ረዳት፤ እና ለልጆች የቤት እንክብካቤ ሰጪዎች ለትምህርት የሚያስፈገው ጨምራል። የጨመረው መመዘኛዎች በልጅነት ያለ እንክባክቤ እና በትምህርት ጥራት ላይ ተጽእኖ የሚኖራቸው የአስተማሪ ብቃቶች መሆኑን የሚያመለክተው ምርምር ላይ መሰረት አድርጓል። የአዲስ ሰራተኛ ብቃቶች በኋላፊነቶች ላይ መሰረት በማድረግ የተለያየዩ የጊዜ ገደቦች ይኖሩታል:
  - የማዕከሉ ርዕሰ መምህራን: በልጆች የልጅነት ጊዜ ትምህርት ባችለር ኦፍ አርት (ቢኤ) ወይም በዲሴምቤር 2022 ላይ ቢያንስ 15 ሴምስቴር ኪሬዲት ሃዎርስ በልጅነት ጊዜ ትምህርት ቢኤ ያለው።
  - አስተማሪዎች: በልጆች የልጅነት ጊዜ ትምህርት (አሶሰዬት ኦፍ አርት (ኤኤ) ወይም በዲሴምቤር 2020 በልጅነት ጊዜ ትምህርት ቢያንስ የ24 ሴሚስተር ኪሬዲት ሃዎር ኤኤ ያለው።
  - ረዳት አስተማሪዎች: በዲሴምቤር 2018 የልጆች ዕድገት አሶሰዬት ያላቸው።
  - የቤት እንብካቤ ሰጪዎች: በዲሴምቤር 2018 የልጆች ዕድገት አሶሰዬት ያላቸው።
  - የቤት እንብካቤ ሰጪዎች: በዲሴምቤር 2018 የልጆች ዕድገት አሶሰዬት ያላቸው።
  - የተስፋፋ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሰጪ: በልጆች የልጅነት ጊዜ ትምህርት (አሶሰዬት ኦፍ አርት (ኤኤ) ወይም በዲሴምቤር 2019 በልጅነት ጊዜ ትምህርት ቢያንስ የ24 ሴሚስተር ኪሬዲት ሃዎር ኤኤ ያለው።

የማዕከሉ ርዕሰ መምህር ሆኖ የሚቀጠር ማንኛም ሰው ወይም እነዚህ ሕጎች ሥራ ላይ በሚውሉባቸው ቀናት በኮሎምቢያ ግዛት በልጅ ዕድገት ማዕከል ላይ ፈቃድ የተሰጠው ብቁ የሆነ አስተማሪ፣ እና በዚህ የኃላፊነት ቦታ ላይ ላለፉት አሥር (10) ዓመታት በቀጣይነት አያገለገለ ያለ፣ ለብቃት ጥያቄዎችን ለማስመስከር ለ OSSE ማመልከት ሊኖርበት ይችላል። ሙሉው የሚያስፈልጉ ነገሮች በ DCMR በ5ሀ §§ ክፍል 164 እስከ 172 ላይ ሊገኝ ይችላል።

- ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት: በእነዚህ በመጨረሻው የሕግ አውጪ ውስጥ ከቀረቡት ከሌሎች በሙሉ ጋር የሚሄድ ፈቃድ ለመስጠት በ OSSE ማመልከቻን በሚመለከቱት በኩል ይወሰናል። ሁሉም የመጀመሪያ እና ከ2, 2016 በፊት የቀረቡ የፈቃድ ማደሻ የ DCMR ምዕራፍ 3 ምዕራፍ 29 ውስጥ በቅድሚያ ሕጎች ውስጥ ይገመገሙ እና፣ ማመልከቻዎች ሕጋዊ የሆነው የተወሰነ ከሆነ፣ ፈቃዱ ለአንድ (1) ዓመት ዋጋ ይኖረዋል። ለእነዚህ መርኃግብሮች፣ የፈቃድ ሰጪ ባለሙያዎች ተጨማሪ የሙያ ድጋፍ እና አዲስ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለማሟላት እንዲረዳቸው ክትትል አገልግሎት ይሰጣል።

OSSE እነዚህም የተሻሻሉ የፈቃድ መስጫ አቅራቦቶችን መፈጸም አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይገነዘባል፤ ነገር ግን OSSE በሙያዊ ድጋፍ፣ በግንኙነት፣ እና በውጤታማ ክትትል በኩል መሰረተ ልማቶቹን ለመርዳት ይተጋል። OSSE ሁሉም የፈቃድ ፈታሾች፣ ፈቃድ ከመስጠት በፊት ፍተሻ የሚያደርጉትን እና የክትትል ጉብኝት የሚያደርጉት፣ መሰረተ ልማቶቹን ለመፈተሽ ብቁ መሆናቸው እና ከጤና እና ለደኅንነት የሚያስፈልጉ ነገሮች ለአገልግሎት ሰጪው ስፍራው ተገቢ ስለመሆኑ እና አገልግሎት ስለሚሰጣቸው ልጆች ዕድሜ ላይ ስልጠና የወሰዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል። በተጨማሪም፣ OSSE መሰረተ ልማቶቹ የሚያግዙትን እና ሀብቶቹን ለመለየት እና ሕጎቹን ውጤታማ ለማድረግ እና ለመጠበቅ እርድታ ለመስጠት ከደንበኞች እና የሕግ ጉዳዮች መምሪያ፣ ከድንገተኛ የእሳት አደጋ እና ከህክምና አገልግሎት ሰጪዎች፣ ከኃይል እና አከባቢ ጉዳይ መምሪያ፣ እና ከጤና መምሪያ ክፍል ጋር እየሰራ ይገኛል።

የመጨረሻው ሕግ አውጪ በግዛቱ ውስጥ የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማትን ለመስራት ፈቃድ ለማግኘት እና በፈቃዱ ለመቀጠል የሥራ ማዕቀፍን፣ እና በሁሉም የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቶች ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ አዲሱ የ CCDBG የሚጠይቃቸውን አካቶ የሚያስፈልግሉ ነገሮች እና መመዘኛዎችን ያስቀምጣል። በ2008፣ በልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቶች ላይ ሕጋዊ የሚጠይቀው ኃላፊነት ከጤና መምሪያ ወደ የ OSSE የሰዎች አገልግሎት ሰጪ ተዘዋውሯል። በዚሁም መሰረት፣ የመጨረሻ ሕግ አውጪበምዕራፍ 3 (የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቶች በሚለው) ውስጥ ከክፍል 300 እስከ 379 ድረስ በ DCMR ርዕስ 29 (የሕዝብ መልካም መሆን በሚለው) የሚያስገድድ እና በ DCMR አዲስ ምዕራፍ 1 (የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቶች: ፈቃድ መስጠት የሚለውን) ከንጹስ ርዕስ ሀ (የትምህርት የመንግሥት የበላይ ባለሥልጣን ቢሮ) ርዕስ 5 (ትምህርት) የሚለውን ይጨምራል ። የ DCMR ምዕራፍ 1 ርዕስ 5 ክፍሎች በሚከተሉት የርዕስ አከባቢዎች የተደራጁ ናቸው:

(1) አጠቃላይ የፈቃድ አሰጣጥ: §§ 100-102 እና § 199
(2) የፈቃድ ማመልከቻ እና ማደሻ: §§ 103-117
(3) ለሁሉም ፈቃድ ጠያቂዎች የሚያስፈግ ነገሮች: §§ 118-121
(4) መሰረተ ልማቶች፣ አቅራቦቶች፣ መሳሪያዎች እና የአከባቢው ጤና: §§ 122-126
(5) አስተዳደር እና ግብረኃይል: §§ 127-131
(6) ሠራተኛ: §§ 132-139
(7) ለጤናማ ዕድገት የሚፈጸሙ ተግባራት: §§ 140-141
(8) የጤና ማስተዋወቅ እና መከላከል: §§ 142-161
(9) ፈቃድ ለተሰጣቸው ማዕከላት ተጨማሪ የሚያስፈልጉ ነገሮች §§ 162-166
(10) ፈቃድ ለተሰጣቸው የልጅ ማሳደጊያ ቤቶች ተጨማሪ የሚያስፈልጉ ነገሮች: §§ 167-168
(11) ፈቃድ ለተሰጣቸው የልጅ ማሳደጊያ የተስፋፉ ቤቶች ተጨማሪ የሚያስፈልጉ ነገሮች: §§ 169-171
(12) ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ላሉት መርኃግብሮች የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ነገሮች: §§ 172-176

ለሕጋዊ ማዕቀፍ ቁልፍ ለውጦች ከዚህ በታች ተብራርተዋል። ከ CCDBG አዋጅ ወይም የአፈጻጸም ደንቦቹ ሥር ለመሆን ለውጥ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ግንዛቤ ውስጥ ገብቷል"***።

አጠቃላይ የፈቃድ አሰጣጦች ላይ የተደረጉ ቁልፍ ለውጦች፡

ከክፍል 100 እስከ 102 ድረስ ለልጅ ዕድገት ፈቃዶችን ለመስጠት አካቶ አጠቃላይ መሪዎችን ይሰጣል፤ ነገር ግን የሚያስፈልጉ ነገሮችን ተግባራዊ መደረጋቸው፣ የፈቃዱ ዓይነት እና ፈቃዱ የሚሰራበት የጊዜ ርዝመት ላይ የተወሰነ አይሆንም።

የማይመለከቱ ነገሮች

የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማትን ለመስራት የልጅ መሰረተ ልማት ትንታኔን ላይ መሰረት በማድረግ ፈቃድ ለመውሰድ የትኞቹ አገልግሎቶች የግድ እንደማያስፈልጉ ለመግለጽ፣ OSSE የግድ የማያስፈሉግ አገልግሎቶችን ዝርዝር ይዘረዝራል። ለልጅ ዕድገት የግድ የማያስፈልጉ ነገሮችን ዝርዝር፣ ለበለጠ መረጃ የ DCMR 5 ሀ § 101ን ይመልከቱ።

የፈቃዱ ዓይነቶች

“ፈቃድ ለማግኘት” ቀደም ተብሎ የተሰቱ ሕጎች። በመጨረሻው የሕግ አውጪ ውስጥ፣ “ሰጪ ፈቃድ” በአሁኑ ጊዜ ጉድለት ላይ ላይ መሰረት ተደርጎ በሚሰጠው ብቸኛ በሆነው ፈቃድ በ"ውስን ፈቃድ" ተቀይሯል። ውስን የሆነው ፈቃድ ለማገኣድ ወይም መሰረተ ልማቱ አንዱ ወይም ብዙው ሲጎድል ነባሩን ፈቃድ ለመሰረዝ እንደ አማራጭ በ OSSE ሊሰጥ ይችላል። ለበለጠ መረጃ፣ የ DCMR 5 ሀ § 102.6ን ይመልከቱ።

የፈቃዶቹ የጊዜ ርዝመት

ቀድሞ የነበሩት ሕጎች ለአንድ ዓመት ፈቃድ ይስጣል። በአዲሱ ሕጎች መሰረት ግን፣ እያንዳንዱ ፈቃድ ለሦስት ዓመት ያህል ሊሰራ ይችላል። የፈቃዱ ጊዜ ከአገሩ ምርጥ ልምምዶች ጋር አብሮ ለመሄድ ተብሎ የጨመረ ሲሆን፣ በጥራት፣ በጤና፣ እና ደኅንነቱ በተጠበቀ እንክብካቤ ላይ ቁጥጥር በማድረግ ላይ ትኩረት ወደማድረግ የመሻገር ሀሳብ ያለው ነው። ለበለጠ መረጃ፣ የ DCMR 5 ሀ § 102.7 ይመልከቱ።

የጥራት ደረጃ እና የማሻሻያ ስርዓት***

]የጥራት ደረጃ እና የማሻሻያ ስርዓት ለልጅ የሚሰጠውን እንክብካቤ መርኃግብሮችን የጥራት ደረጃን በመመደብ እና የጥራት ማሻሻያ ድጋፎችን በመስጠት በልጅነት ያለውን እንካቤ እና ትምህርትን ጥራት ለመለካት እና ለማሻሻል ይረዳል። ሁሉም ፈቃድ የተሰጣቸው የሕዝብ ገንዘብ ድጋፍ ያገኙ መሰረተ ልማቶች በ OSSE'የጥራት ደረጃ እና የማሻሻያ ስርዓት ውስጥ መሳተፍ የግድ ይላቸዋል። ማንኛውም ፈቃድ ያለው መሰረተ ልማት ነገርን ግን የሕዝብ የገንዘብ ድጋፍ ያልተቀበለ ከሆነ እንደ አማራጭ በየጥራት ደረጃ እና የማሻሻያ ስርዓት ውስጥ መሳተፍ አለበት። ለበለጠ መረጃ፣ የ DCMR 5ሀን §§ 102.8 እና 102.9 ይመልከቱ።

ለፈቃድ ማመልከቻ እና ማደሻ ቁልፍ ለውጦች፡

የ DCMR 5ሀ §§ 103-117 የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማትን ለመስራት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ማመልከቻዎችን ስለመስጠት፣ ስለ እድሳት፣ እና የማካተት ፈቃድ አካቶ ፈቃድ እንዴት እንደሚያገኙ እና እንደሚያቆዩ፣ OSSE ውስን የሆነ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ፈቃዱ ከሚጠይቀው ነገሮች አቤቱታ የማቅረቢያ ሂደትን፣ እና አዲሱን ፈቃድ የሚጠያቸውን የመሰረተ ልማት ለውጦችን ዓይነት ማጠቃለያ እንዴት እንደሆነ ይገልጻል። በተጨማሪም ፣ እነዚህ ክፍሎች ፈቃድ ስላገኙ ክፍያዎችን፣ ዓመታዊ ቁጥጥርን እና ምርመራን በተመለከተ በ CCDBG አዋጅ እንደሚጠይቀው አቅራቦትን የሚሰጥ ሲሆን፣ የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማት የድርጊት ማብቃት ገለጻ በሕጎቹ ግዳጅ በለመወጣት ላይ ይውሰናል።

ለማመልከቻ የሚያስፈልጉ ዶመንት

የ DCMR 5ሀ § 103 የልጅ እድገት መሰረተ ልማትን ለመስራት በመጀመሪያ ማመልከቻ በሚያቀርብበት ጊዜ ጠያቂዎ ሊያካትታቸው የሚገባውን ዶክመንቶች፣ ተገቢ የሆነ የመድኅን ዋስትና ማረጋገጫ እና ቦታን እንደ ቀብድ ለመያዝ ሕንጻን ለመጠቀም ያለ የስምምነትን ወረቀትን አካቶ ይጠይቃል። የልጆችን ደኅንነት እና መረጋጋትን ለማረጋገጥ፣ ፈቃድ ተቀባይ ለሰላሳ ቀን ለማይበልጥ ለጊዜያዊነት ስዘጋ አገልግሎት የሚሰጥ የተገለጸ ተጠባባቂ ቦታን ማመልከት ሊጠበቅበት ይችላል። ተጠባባቂ ቦታን ለማግኘት የሚያስችል ተገቢነት ያለው የሕንጻ አጠቃቀም ስምምነት ምንም እንኳን ፈቃድ የተሰጠው መሰረተ ልማት ጥቅም ላይ በማይውልበት ጊዜ ፈቃድ የተሰጠው ሰው እንክብካቤ እና ትምህርት በመሰጠት እንዲቀጥል በመፍቀድ የድንገተኛ ሁኔታዎች በሚገጥሙበት ጊዜ ለልጆች እና ለሠራተኞች መረጋጋትን ለመስጠት አስፈላጊ ነው።

ሌላ ነገር በፈቃዱ ላይ ለማካተት የሚቀርብ ማመልከቻ

የመጨረሻው ሕግ አውጪ ሌላ ነገር ላይ በፈቃዱ ላይ እንዲካተት ለማመልከት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ይገልጻል። ሌላ ነገር በፈቃዱ ውስጥ ለማካተት የሚውል ማመልከቻ ለተመሳሳይ ምልከታ እና ለመጀመሪያ ጊዜ ወይም ለፈቃድ እድሳት ማመልከቻ ለማቅረብ የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ OSSE አስፈላጊ ነው ወይም ይጠቅማል ብሎ ከወሰነ የኢንተርኔት ላይ ፍተሻን በማካተት ላይ በመስረት ይደረጋል። ለበለጠ መረጃ፣ የ DCMR 5 ሀ § 105 ይመልከቱ።

ከፍያ እንዳይኖር ማድረግ

የመጨረሻዊ ሕግ አውጪ ከማውጣቱ በፊት፣ ለፈቃድ ወሳጆች እና ለአመልካቾች የማለሳስለ ነገር የሚቻለው ከሕግ ጋር በተያያዘ ለአካላዊ ወይም ለመዋቅራዊ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሲለያዩ ነው። ሆኖም ግን፣ የ DCMR 5ሀ § 106፣ ለ OSSE ባለሥልጣን ለማንኛውም የፈቃድ አሰጣጥ የልጆችን ወይም የሠራተኞችን ጤንነት፣ ደኅንነት፣ ወይም በመልካም ሁኔታ መሆንን የማይከለከለውን ነገር ላይ የክፍያ ቅነሳ ይሰታል። ሁሉም አዲስ እና ነባር መሰረተ ልማቶች በ DCMR 5ሀ § 106 ላይ እንደተቀመጠው ገንዘብ ቅነሳ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል። OSSE ወደፊት ሕግ የሚያወጡትን መረጃ ለመስጠት በቅነሳ በኩል የተገኘውን መረጃ ይጠቀማል።

የፈቃድ መስጫ ጊዜ እና

የ OSSE ክፍያዎች ዲሴምቤር 2, 2016 ላይ እና በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ እና ለእድሳት ማመልከቻ ላቀረቡ አመልካቾች የፈቃድ ጊዜው ከአንድ ዓመት ወደ ሦስት ዓመት ተራዝሞላቸዋል። ሆኖም ግን፣ የፈቃድ ጊዜ ረዥም ከመሆኑ የተነሳ፣ የፈቃድ ክፍያዎች ጨምረዋል። የአዲሱ ፈቃድ ክፍያ መጠን በለፈቃዱ የተሰመደውን በዓመት የሚከፍለውን የፈቃድ ክፍያውን በሦስት በማባዛት ይሆናል። ፈቃዱ ውስጥ ሌላ ነገር ለማካተት ወይም ፈቃዱን ለመለወጥ ተጨማሪ ክፍያዎች ይኖሩታል። OSSE ፈቃዱን ወደ ሦስት (3) ዓመት መለወጥ በገንዘብ በኩል በመሰረተ ልማቶቹ ላይ ተጽእኖ እንደሚኖረው ይገነዘባል። መሰረተ ልማቶቹን በሁለቱም በፈቃድ እና በማመልከቻ ክፍያዎች ወጪ ለመርዳት፣ OSSE መሰረተ ልማቶቹ የክፍያ ዕቅድ ስምምነትን እንዲያስቀምጥ ይፈቅዳል። እባክዎትን ለበለጠ መረጃ፣ የ DCMR 5ሀ § 108ን ይመልከቱ።

የተጠቃሚዎች ትምህርት ***

የ CCDBG አዋጅ እንደሚጠይቀው፣ የ DCMR 5ሀ § 111.9 OSSE ከሴፕቴምቤር 30, 2017 በፊት፣ ሁሉንም ፈቃድ ያላቸውን መሰረተ ልማቶች፣ ለእያንዳንዱ መሰረተ ልማት የሚከተሉትን መረጃዎች አካቶ፣ ለሕዝብ በኤሌክትሮኒክ ማቅረብ እንዳለበት ያስገድደዋል።

- የመቆጣጠሪያ እና የመፈተሻ ቀናት
- የመቆጣጠሪያ እና የመፈተሻ ውጤት ሪፖርቶች፡
- ማንኛውም የተወሰደ የእርምት ወይም የማብቃት ሥራ፡
- ይህ ምዕራፍ ከሚሰጠው ወይም እንደዚያ ዓይነት ማካተት፣ እና ሌሎች የፌዴራል እና የአከባቢ ሕግ እና ደንቦች ጋር ለመሄድ ባለመቻሉ ተጨባጭ ቅሬታዎች በሚቀርቡበት ጊዜ፣ እና
- የሞት ቁጥር፣ ከፍተኛ ጉዳቶች፣ እና በእያንዳንዱ መሰረተ ልማት የተከሰተውን ተጨባጭ የሆነ የልጆች መጉዳት ምሳሌዎች

የማብቃት ሥራዎች

የ DCMR 5ሀ §§ 112 እስከ 117 ድረስ ለሁሉም የማብቃት ሥራዎች መሰረተ ልማቱ፣ አስቀድሞ ካለው የሕግ ማዕቀፍ ጋር ወጥ ሆኖ የሚቀረውን የበላይ ሰጪዎችን ያስቀምጣል። OSSE እያንዳንዱን ተግባር እንዴት መጠቀም እንደሚችላ ግልጽነትን ለመስጠት ቋንቋን የጨመረ ሲሆን የቀደመው ፈቃድ ከተሰረዘ የቅርብ ጉድቱን እና ለሦስት (3) ዓመት እንደገና የማመልከትን ክለከላ ምሳሌዎችን ጨምሯል። ለበለጠ መረጃ የ DCMR 5ሀን §§ 112 እስከ 117 ድረስ ይመልከቱ።

ለሁሉም ለፈቃዱ ባለቤቶች የሚያስፈልጉ ቁልፍ ለውጦች

የ DCMR 5ሀ §§ 118 እስከ 121 ለሁሉም ፈቃድ ለተሰጣቸው የልጅ እድገት መሰረተ ልማቶች፣ በተለይም ለቁጥጥር እና የአዋቂ እና የልጅ ሬሾ እና የቡድን መጠን፣ የሚያስፈልጉትን ተዋረድ ያስቀምጣል።

በመጨረሻው የሕግ አውጪው ሕግ ሥር፣ ማንኛውም ተጨማሪ በተለይም ለልጆች ዕድገት ማዕከላት፣ ቤቶች እና የተስፋፉ ቦቶች፣ ወይም ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ያሉት መርኃግብሮች የሚጠየቁ ነገሮች፣ በቀጣይ ክፍሎቻቸው ውስጥ ይገኛሉ። በተጨማሪ ስለሚጠየቁ ነገሮች ለበለጠ መረጃ፣ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመልከቱ፡

- የልጅ ዕድገት ማዕከላት፡ የ DCMR 5ሀን §§ 162 እስከ 166 ድረስ ይመልከቱ።
- ለልጅ ዕድገት ቤቶች፡ የ DCMR 5ሀን §§ 167 እስከ 168 ድረስ ይመልከቱ።
- ለልጅ ዕድገት የተስፋፉ ቤቶች፡ የ DCMR 5ሀን §§ 169 እስከ 171 ድረስ ይመልከቱ።
- ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ላሉት መርኃግብሮች፡ የ DCMR 5ሀን §§ 172 እስከ 176 ድረስ ይመልከቱ።

የእረፍት ጊዜ ሬሾ

በማይጨናነቅበት ሰዓት ወይም እንቅልፍ ሽለብ በሚያደርግበት ወይም በእረፍት ጊዜ የሚጠየቀውን ሬሾ ለመግለጽ፣ የ DCMR 5ሀን §§ 121 የአዋቂዎች እና የልጆች ሬሾ መጠበቅ እንዳለበት ያዛል፤ ሆኖም ግን ሌላ አዋቂ የሠራተኛው አባል ወይም አዋቂ በጎ ፈቃደኛ ለአንድ (1) የተገለጸ የሠራተኛው አባላት መተካት አለበት፤ ቢያንስ አንድ 91) አስተማሪ ወይም ረዳት አስተማሪ ቡድኖቹን ለመምራት መሰጠት አለበት። በተጨማሪም፣ የተለያዩ ዕድሜ ያላቸው ልጆች በሰላሳ (30) ወራት ውስጥ በየትኛውም እድሜ ውስጥ ያሉት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ቡድኖች ለእረፍት እንቅልፍ በአንድ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ፣ አንድ (1) የሠራተኛ ሰው በሚያያቸው ቦታ ላይ መሆን እና የልጆቹንም ድምጽ ሁሉ ጊዜ መስማት አለበት። ሁለተኛው ሠራተኛ የሆነ ሰው ወይም በጎ ፈቃደኛ የሚሰጥ ሰው በመሰረተ ልማቱ ላይ በተመሳሳይ ወሌል ላይ መገኘት እና ድንገተኛ የሆነ ነገር በሚገትምበት ጊዜ ለመርዳት መገኘት አለበት።

ለመሰረተ ልማቶቹ፣ ለአቅራቦቶቹ፣ ለመሳሪያዎቹ እና ለአከባቢው ጤና ቁልፍ ለውጦች፣

የ DCMR 5ሀን §§ 122 እስከ 126 ድረስ ለልጅ ዕድገት መሰረተ ልማት የሚገባውን ጤናማ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ መመዘኛዎችን፣ በተለይም የመታጠቢያ ቦታውች እና መሳሪያዎች፣ በቤት ውስጥ ያሉትን አከባቢዎች መመዘኛ በመስጠት እያንዳንዱ ደኅንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን እና ለነጻ እንቅስቃሴ እና እንቅስቃሴ ላለው ጫዋታ ተገቢ የሆነ ቦታን፣ ከቤት ውጪ ያለውን አከባቢ እና የመጫወጫ ቦታን፣ እና መሳሪያዎች፣ ማቴሪያሎችን እና መሰረተ ልማቶቹ በሚሰሩበት ጊዜ ጥቅም ላይ ለሚውሉት ማስዋቢያዎች መመዘኛዎችን በመስጠት አስቀምጧል።

ከእሳት አደጋ የመጠንቀቅ ፍተሻዎች

የ DCMR 5ሀን §§ 122.6 ሁሉም መሰረተ ልማቶች በእሳት አደጋ የመጠንቀቅ ፍተሻዎች ሥር ማለፍ እንዳለባቸው እና መሰረተ ልማቱ ለእሳት አደጋ ጥናቄ እና ለተያዥ ኮዶች በሙሉ ተገቢ መሆኑን የሚያረጋግጠውን ሰርቴፊኬት ከ FEMS መውሰድ እንዳለባቸው ያስገድዳል። አስቀድሞ፣ የልጅ ዕድገት ቤቶች ዓመታዊ የእሳት ፍተሻ የማግኘትን ግድታ አያስቀምጥም ነበር። በተጨማሪም፣ ዕድሜያቸው ከ30 ወራት በታች የሆኑ የሚገቡ ልጆች ቁጥር ከጨመር ይህ ደግሞ በመሰረተ ልማቱ ደኅንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በርካታ ልጆችን የማገልገል አቅሙ ላይ ተጽእኖ ስለሚያደርግ እና ለድንገተኛ አደጋ የሚያባብስ ስለሆነ፣ መሰረተ ልማቱ አዲስ የእሳት መፈተሻ፣ እና የሚይዘውን መጠን የሚያሳይ ሰርቴፊኬት ሊይገኝ ይገባል። እባክዎትን የመጀመሪያው የፍተሻው ወጪ በ OSSE እንደሚሸፈን ይወቁ፤ ሆኖም ግን፣ የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቶች ለማንኛውም አስፈላጊ ለሆነ ጥገናዎች ኃላፊነቱን ይወስዳል። ለበለጠ መረጃ የ DCMR 5ሀን [4]§§ [5]122.6 እስከ 122.7 ድረስ ይመልከቱ።

ነፍሳት እና ተባይ መቆጣጠር

የ DCMR 5ሀን [4]§§ [5]122.19 እስከ 122.21 ድረስ ፈቃዱ የመሰረተ ልማቱ ምቹነት ከነፍሳቶች፣ ከትናናሽ ተዋዕስያን፣ እና ሌሎች ተባዮች እና ከጥገኛ ነፍሳቶች፣ ትናንሽ ተዋዕስያን፣ እና ሌሎች ተባዮች ነጻ መሆኑ ማረጋገጥ እንዳለበት ያስቀምጣል። ይህ አዲስ ክፍል ልጆች ጤናማ እና ከማንኛውም ሊጎዳቸው ከሚችል ወይም ከሚያሳምማቸው ነገሮች ነጻ የሆነ ደኅንነቱ የተጠበቀ አከባቢ ላይ እንክብካቤ መቀበላቸን ለማረጋገጥ በአዲሱ ሕጎች ውስጥ ተጨምሯል። ፈቃድ የወሰደ ሰው ነፍሳትን፣ ተዋዕሳኒያንን፣ እና ሌሎች ተባዮችን ለመቆጣጠር በምርጥ መንገድ ለመፈጸም እና በመሰረተ ልማቱ ውስጥ ተባይ የሚገኝበት ቦታን፣ የሚራቡበትን ቦታ፣ እና የሚያጠቁበትን ቦታ ለመከላከል እና ለማጥፋት የማጥፊያ መንገዶችን ሊኖሩት ይገባል። የነፍሳት፣ የተዋዕስያን፣ ወይም ሌሎች ተባዮች የሚገኙበት፣ የሚረቡበት እና ሰዎችን የሚናደፉበት በመሰረተ ልማቱ ላይ የሚከሰት ከሆነ፣ ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ ወዲያውኑ እንዳልተለመደ አጋጣሚ ለ OSSE ስለተባይ ጥቃቱ ሪፖርት ማድረግ እና ነፍሳትን፣ ተዋዕስያንን፣ ወይም ሌሎች ተባዮችን ከመሰረተ ልማቱ ለማጥፋት ወዲያውኑ እርምጃ መውሰ አለበት። በተጨማሪም፣ ፈቃዱ የተሰጠው ግለሰብ በመሰረተ ልማቱ ላይ ስለ ተባይ ማጥፋቱ አገልግሎቶች ጥቅም፣ ፈቃድ ባለው የተባይ ማጥፊያ ባለሙያ የሚሰጠውን የተመዘገበ ዶክመንት ሊኖረው ይገባል። የጸረ ተባይ መድኃኒት በሚረጭበት ጊዜ ወይም መድኃኒቱ በተደረገ በሃያ አራት ሰዓታት (24) ውስጥ ልጆች እዚያ መገኘት የለባቸውም።

የራስ መከላከያ ኮፊያ

በልጆቻችን እንክብካቤ ሰጪ ሀሳብ እንደሚሰጠው፣, የ DCMR 5ሀ § 126.22 ልጆች ጎማ ያላቸውን መሳሪያዎች የሚነዱ ከሆነ፣ በልጆች ዕድገት መሰረተልማቶች ውስጥ እንክብካቤ በሚደረግበት ጊዜ የልጆቹ ደኅንነት ለማረገገጥ የራስ መከላከያ ኮፊያ መልበስ የግድ ነው። መሳሪያዎቹ የሚነዱት ቤት ውስጥ ይሁን ወይም ከቤት ውጭ ጎማ ያላቸው መሳሪያዎች ባለ ሦስት ጎማ ብስክሌቶች፣ ብስክሌቶች፣ መንሸራተቻዎች፣ የመንሸራተቻ ጫማዎች፣ ከብረት የተሰራ በረዶ ላይ የመንከባለያ ወይም መንሸራተቻን የሚያሟሉ መሆን አለባቸው። የራስ መከላከያ ኮፊያዎች በትምህርት ቤት፣ በወላጆች፣ ወይም በእርዳታ የተሰጡ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን በየ DCMR 5ሀ § 126.11 ላይ የተቀመጠውን ማሟላት አለባቸው።

ለአስተዳደር እና ለግብረኃይል ቁልፍ ለውጦች

የDCMR 5ሀ §§ 127 እስከ 131 ለልጅ አስተዳደግ መሰረተ ልማት አስተዳደር እና ድርጊት፣ የሚፈለገውን የመሰረተ ልማቱን ግንኙነት ምን ማሟላት እንዳለበት አካቶ ያስቀመጠ ሲሆን ለወላጆች እና ለአሳዳጊዎች፣ ያልተለመዱ ክስተቶችን ሪፖርት ለማድረግ፣ እና ለመሰረተ ልማቱ የሚያስፈልጉ ጽሑፎችን፣ የሠራተኞች መዝገቦች እና የልጆች መዝገቦችን ይሰጣል።

ለሠራተኞች ቁልፍ ለውጦች፡

የDCMR 5ሀ §§ 132 እስከ 139 ለሁሉም የሠራተኞ አባላት፣ የቀድሞ የወንጀል ታሪክ ፍተሻን፣ የትራፊክ መዝገብ ፍተሻ፣ እና ስለ አደንዛዥ ዕጽ እና የአልኮል ፍተሻን አካቶ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ላይ መፍትሔ ይሰጣል። [1]የDCMR 5ሀ [2]§§ 138 ለአደጋ ጊዜ የመጀመሪያ እርዳታን እና ለበጎ ፈቃደኞች፣ የበጎ ፈቃደኞችን እና የሚያስፈልጉ የቅድመ ሁኔታ ፍተሻ ሥራዎችን አካቶ የተለያየዩ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያስቀምጣል። የDCMR 5ሀ §139 ለሚከፈላቸው የሠራተኞች አባላት የሙያ ዕድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያስቀምጣል።

የቀድሞ የወንጀል ታሪክ ፍተሻዎች***

ክፍል 133 ለሁሉም የሠራተኞች እና ለበጎ ፈቃደኞች የቀድሞ የወንጀል ታሪክን ለመፈተሽ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ያስቀምጣል። የCCDBG አዋጅ፣ እና የደንቦቹ አፈጻጸም፣ ሁሉም የልጅ እንክብካቤ ሰጪ ሠራተኛ አባላት (በቀጣይነት የሚቀጠሩ የሠራተኛ አባላትን አካቶ) እና ሁሉም ፈቃድ ያላቸው በጎ ፈቃደኞች፣ በእንክብካቤ ሰጪነታቸው ለሁሉም ልጆች ጋር የተያያዘ ካልሆነ፣ በሕግ ለሚታወቁ፣ ለተመዘገቡ የልጆች እንክብካቤ ሰጪዎች አጠቃላይ የቅድመ ሁኔታ ፍተሻ መስጠት እንዳለበት ያስገዳድል። OSSE በዚህ ክፍል ውስጥ ለተከፋይ የሠራተኞች አባላት ለሁሉም የቀድሞ የወንጀል ታሪክ ፍተሻዎች የማደሻ የጊዜ ገደብ ሦስት (3) ዓመት መሆኑን ይገልጻል። አጠቃላይ የቅድመ ታሪክ ፍተሻ ከመቅጠር በፊት የሚደረግ እና ፈቃዱ በተሰጠበት ጊዜ በእያንዳንዱ 3 ዓመት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ መደረግ አለበት።

በደንቦቹ እንደተገለጸው፣ በጎ ፈቃደኛ በመሰረተ ልማቱ አገልግሎት ሰጪ ክፍያ የማይሰጠው ለልጅ ዕድገት መሰረተ ልማት አገልግሎቶችን የሚሰጥ፣ ለሥራ ልምድ አገልግሎት የሚሰጥን ወይም በትምህርታዊ ወይም በሥልጠና መርኃግብር ሥር የሚሰራ ሰውን ነው። በጎ ፈቃደኞች ለመስክ ጉዞ፣ ለድግስ፣ ወይም ለተለዩ በዓላት የሚሰጠውን አያካትትም። ሆኖም ግን፣ በማንኛውም ጊዜ የቀድሞ ታሪኩ ወንጀል ፍተሻ ስር ያላለፈ የበጎ ፈቃደኛ ያልሆነ ልጆችን ለመቆጠጠር አይችልም። የበጎ ፈቃደኞች በየሁለት (2) ዓመቱ የሚደረግ የወንጀል ምርመራ እንዲኖራቸው ይገደዳሉ።

ሁሉም የቀድሞ ፍተሻዎች የብሔራዊ የወንጀል መረጃ ማዕከልን (FBI)፡ የ FBI የጣት አሻራ ፍተሻ (የቀጣዩን ትውልድ መታወቂያን በመጠቀም፣ የብሔራዊ የግብረስጋ ግንኙነት ወንጀል ምዝገባን፣ ላለፉት አምስት ዓመታት አመልካቹ የኖረባቸውን የሁሉንም የግዛቱ የወንጀል እና የግብረስጋ ግንኙነት ወንጀል ምዝገባ፣ ላለፉት አምስት ዓመታት አመልካቹ የኖረባቸውን የሁሉንም የግዛቱ የልጅ እንግልት እና ቻላ ማለት መዝገብ፣ እና የልጅ መከላከል ምዝገባ (በዲሲ የልጅ እና የቤተሰብ አገልግሎት ኤጀንሲ የሚመራው) መዝገብ ውስጥ መመርመርን ያካትታል።

በተጨማሪም፣ ለልጆች የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ሞተር ሳይክል የሚነዱ የሠራተኛ አባላት የትራፊክ መዝገብ ላይ የመፈተሽ አጋጣሚ ይሆኖራቸዋል። ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎትን የ DCMR 5ሀ § 134 ይመልከቱ። የአደንዛዥ ዕጽ እና የአልኮል ምርመራ

የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማብራራት በግዛቱ ሕግ ሥር የተቀመጠው፣ የD-CMR 5ሀ § 136 የአደንዛዥ ዕጽ እና የአልኮል ምርመራን መመሪያዎች እና ሥርዓቶችን በቀጥታ ከልጅ ጋር ግንኙነት ያላቸው በልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩት ሠራተኞች በሙሉ፣ በቀጥታ ለልጆች እንክብከቤ የሚሰጡት፣ እና በየዕለቱ የሚሰራው ሥራው የልጆችን ጤና፣ መልካም አኗኗር፣ ወይም ደኅንነት ላይ ተጽእኖ የሚያደርሱ እንዲኖራቸው ያስገድዳል፤ ያም በሚከተሉት ጊዜያት ፍተሻ ማድረግን ያካትታል

- ከመቀጠር በፊት፡
- ምክንያታዊ በሆኑ ጥርጣሬዎች ላይ በመመስረት፡ እና
- በተቻለ ፍጥነት ምክንያታዊ የሚሆኑ አጋጣሚዎችን በመከታተል።

እነዚህ ሁኔታዎች፣ በልጅ እና በወጣት፣ በደኅንነት እና በጤና የአምኒባስ የተካተተው አዋጅ 2009 ላይ የግድ ስለሚል አዲስ መመዘኛዎች አይደሉም፤ ሆኖም ግን የመጨረሻው የሕግ አውጪ ሕግ በግዛቱ ሕግ ውስጥ የተቀመጠውን መመዘኛዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያዛል።

የሠራተኛ አባል ግዴታዎች

የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማት የሆነ እያንዳንዱ የሠራተኛ አባል ልጆችን ለመንከባከብ በሰውነት ብዙ የሆነ፣ እና የሠራተኛው አባል የሳንባ ነቀርሳ የሌለው መሆኑን ወይም ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የሌለው መሆኑን የሚያሳይ፣ እና እርሱ ወይም እርሷ ልጆችን ለመንከባከብ በአካል ብቁ መሆኑን/ኗን የሚያሳይ የጤና እንክብካቤ ሰጪ የሰጠው የዓመታዊ የጤና ምርመራ ወረቀት ሊኖረው ይገባል። የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ብቻ በየዓመቱ የማድረግ ግዴታ አለው። ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎትን DCMR 5ሀን § 137 ይመልከቱ.

የጤና እና የደኅንነት ስልጠና እና የሙያ ዕድገት***

የDCMR 5ሀን § 139 ለተከፋይ የሠራተኛ አባል የሙያ ዕድገት ግዴታዎ ችን ያስቀምጣል። ሁሉም ተከፋይ የልጅ ዕድገትን መሰረተ ልማት ለመስራት ፈቃድ ያላቸው ሥራቸው ወይም ኃላፊነታቸው የልጆች እንክብካቤን የሚያካትት ሠራተኞች አገልግሎቱን ከመስጠት በፊት እና የቃል ማስተዋወቂያ ሥልጠና ውስጥ መግባት አለባቸው፤ እንዲሁም በቀጣይነት በሚኖረው በዓመታዊው የጤና እና የደኅንነት አጠባበቅ ሥልጠ፣ እና የሙያ ማሳደጊያ ውስጥ መሳተፍ አለባቸው።

ቅድመ አገልግሎት***: በተቀጠሩ በ30 ቀናት ውስጥ፣ ሥራው ወይም ኃላፊነቶቹ ልጆች እንክብካቤ ውስጥ የሚያስገባው ሠራተኛ የጤና እና የድኅንነት ጥበቃ ከሚከተሉት ጋር የተያያዘ ሥልጠና መውሰድ አለበት፡

- መከላከል፣ ጥቆማ፣ እና የልጆችን መጎሳቆል እና ችላ መባልን ሪፖርት ማድረግ ላይ
- በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ዝግጅት እና ለምላሹ ማቀድ፡
- ድንገተኛ የሆነ የሕጻናት ሞትን መከላከል እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የእንቅልፍ ልምምድ (በልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቱ የሚገለገሉት ልጆች ዕድሜ ተገቢ ከሆነ)፡
- የሚፈሩ ልጆችን ስጋት እና የተጎሳቆለ የጭንቅላት ሰቀቀን መከላከል (በልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቱ የሚገለገሉት ልጆች ዕድሜ ተገቢ ከሆነ፤ እና
- የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ እና CPR

በተጨማሪም፣ የፌዴራሉ ደንብ ለልጆች በቀጥታ እንክብካቤ የሚሰጠው የሠራተኛ አባላት ተላላፊ በሽታዎችን፣ መመረዝ ለመከላከል፣ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የእንቅልፍ አተኛነት ልምምድ እና የልጆች ፍርሃትን/የጭንቅላት መጎሳቆል ሰቀቀን፣ አገልግሎቱን የሚያገኙት ልጆች ዕድሜ ለዚህ ተገቢ ከሆነ ለመከላከል ሥልጠና ወስደው እስከሚጨርሱ ድረስ በልጆች የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ሰጪ ሃኪም እና በ CPR ቁጥጥር ሥር መሆን እንዳለባቸው፣ ይህ ግዴታ በ DCMR 5ሀ§ 139.2 ውስጥ ተቀምጧል።

የማስተዋወቂ ሥልጠና***:

በተጨማሪም፣ እነዚያ ሥራቸውን እና ኃላፊነታቸው የልጆችን እንክብከቤን የሚያካትት ሠራተኞች ተጨማሪ የጤና እና የደኅንነት አጠባበቂ ሥልጠና በተቀጠሩ በ90 ቀናት ውስጥ እንዲወስዱ ይገደዳሉ። ይህ ተጨማሪ ሥልጠና የሚያካትተው፡

- ለሕጻናት፣ በጋሪ ለሚገፉ፣ ትምህርት ቤት ላልገቡ፣ እና/ወይም ለትምህርት የደረሱ ሕጻናት፣ ተገቢነት ካለው ለእድገት ተገቢ የሆኑ ፕሮግራሞች ላይ፤
- ኢንፌክሽን በሚያመጡ በሽታዎችን መከላከል እን መቆጣጠር፣ ክትባቶችን አካቶ፤
- መድኃኒትን ማስተዳደር፣ ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ ስምምነት ጋር በተያያዘው ለመመዘኛው ውጥነት ማሳየት፤
- ከምግብ እና ከሰውነት መቆጣት ለሚመጣ ድንገተኛ ችግሮችን መከላከል እና ምላሽ መስጠት ላይ፤
- የሕንጻ እና የአካላዊ በትክክል ደኅንነቱ የተጠበቀ መሆን፣ ልጆችን ከአደጋ ማለትም ከኤልክትሪክ አደጋ፣ ከውኃ አካላት፣ እና ከተሽከረካሪዎች አደጋ መለየት እና መከላከልን፣ እና
- አደገኛ የሆኑ ዕቃዎችን አያያዝ እና አቀማመጥ፣ እና ተገቢ የሆነ የተበላሹትን የማወገዳ መንገድ።

ቀጣይነት ያለው ዓመታዊ የጤና እና የደኅንነት አጠባበቅ ሥልጠና፣ እና የሙያ ማሻሻያ***: ሠራተኞች በዓመታዊ የሙያ ማሻሻያ፣ የጤና እና የደኅንነት አጠባበቅ መመዘኛዎችን የሚያስጠብቁት እና የሚያሻሽሉት ሥልጠናዎችን የሚያካትተውን ዓመታዊ ሥልጠናን ውስጥ መሳተፍ አለባቸው***፤ እንደሚከተለው ይሆናል፡

- የልጅ ዕድገት ማዕከል ሠራተኛ ቢያንስ 21 ሰዓታት የሚፈጀውን የዓመታዊ የሙያ ማሻሻያ ውስጥ መሳተፍ አለበት፤
- የማዕከሉ ርዕሰ መምህራትን 21 ሰዓታት የሚፈጀውን የፕሮግራም አስተዳደር፣ የሥራ አተገባበሮች፣ እና ግምገማዎችን የሚመለከት ላይ ሥልጠና እንደሚወስድ ይጠበቃል፤
- የልጅ ዕድገት ቤት ለቤት እንክብካቤ ሰጪዎች እና ሠራተኞች በዓመት ቢያንስ 21 ሰዓታት ያህል የሙያ ማሻሻያ ጅልጠና መውሰድ ያለባቸው፤ ሲሆን
- የተስፋፉ የቤት ለቤት የእንክባካቤ ሰጪዎች እና ሠራተኞች በዓመት ቢያንስ 15ሰዓታት ያህል የሙያ ማሻሻያ ጅልጠና መውሰድ አለባቸው።

ስለ ሙያ ማሻሻያ ያሉትን አስገዳጅ ሁኔታዎችን በተመለከተ የበለጠ መረጃ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎትን የDCMR 5ሀ §§ 139, እና 164 እስከ 171 ያለውን ይመልከቱ።

ለጤና ማስተዋወቂያ እና መከላከያ ቁልፍ ለውጦች

የDCMR 5ሀ §§ 142 እስከ 161 ልጆችን ለመከላከል በቦታው ላይ የሚኖር፣ ምንም ዓይነት መሰረተ ልማት ውስጥ ቢሳተፉም፣ ይህ አስገዳጅ ሁኔታዎ ችም፣ ከሌሎች አስገዳጅ ሁኔታዎች መካከል፣ የእጅ ንጽሕናን፣ የዲያፔር፣ ደኅንነቱ የተጠበቀ እንቅልፍ እና የእረፍት ልምምድንም፣ የልጆችን መጎዳ ቆል እንዴት መከላከ እንዳለበት፣ የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ዝግጁነት፣ የመጀመ ሪያ ደረጃ እርዳታ እና CPR፣ ከህመም የተነሳ ራስን መሳት፣ የክትባት መመ ዘኛዎች፣ የመድኃኒት አስተዳደርን፣ ለምግብ አለርጂ መሆን የሚኖፍ ምላሽ፣ የምግብ አገልግሎትን እና የሕጻናት አመጋገብን አካቶ መሰረታዊ የጤና መመ ዘኛዎችን ያስቀምጣል። በዋና ጊዜ እና በውኃ ላይ ጫወታ ጊዜ፣ በትራንስፖ ርት፣ ከቤት እንሰሳት እና ከሌሎች እንሰሳት ጋር በሚገናኙበት ጊዜ፣ ባሕላዊ ባልሆነ አከባቢ ስለሚኖር እንክብካቤ፣ እና የተለየ ፍላጎት ላላቸው ልጆች እንክብካቤ የማድረግ ግደታዎችም በDCMR 5ሀ §§ 142 እስከ 161 ውስጥ መፍትሄ ተሰጥቶባቸዋል።

የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ዝግጁነት እና ምላሽ ለመስጠት ማቀድ***
በCCDBG አዋጅ፣ 5A DCMR § 148 ላይ እንደሚያስገድደው የልጅ ዕድገት መሰረተ ልማቶች ፈቃድ ያላቸው የአደጋ ጊዜ እና የችግር ጊዜ እቅዶች እንዲኖራቸው የሚበልጥ አስፈላጊ ነገሮች ያስቀምጣል። የድንገተኛ አደጋ ጊዜ እና የችግር ዕቅድ በመሰረተ ልማቱ ላይ በሚታይበት ቦታ ላይ መለጠፍ ያለበት ሲሆን፣ በየዓመቱ መመልከት እና መሻሻል አለበት። በተጨማሪም፣ በየዓመቱ ሠራተኞች ከዕቅዱ ጋር የተያያዘ ሥልጠና መውሰድ አለባቸው፤ ወላጆች እና አሳዳጊዎችም በእቅዱ ላይ መረጃዎችን እና የቅርብ መረጃዎችን መቀበል አለባቸው። OSSE በየዓመቱ ለሁሉም ለአገልግሎቱ አቅራቢዎች ይህን ሥልጠና ያዘጋጅ እን ይሰጣል። ተጨማሪ መረጃ ምናልባትም በ DCMR 5ሀ § 148 ላይ ይገኛል።

ክትባት***

በCCDBG አዋጅ፣ DCMR 5ሀ § 152.2 እንደሚያስገድደው ቤት አልባ ለሆኑ ልጆች እና በግዛቱ ውስጥ እንክብካቤ እያገኙ ያሉት ልጆች ይክትባት ወረቀታቸውን እንዲያቀርቡ የ60 ቀን የጸጋ ጊዜ ይሰጣል።

የመድኃኒት አስተዳደር

በልጆቻችን እንክብካቤ ማድረግ አዋጅ , DCMR 5ሀ § 153 አስተየት እንደተ ሰጠው አዳዲስ ግዴታዎች
ወላጅ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ባለፈቃዱ ለልጆች እንክባካቤ መድኃኒትን ማስተዳደር እንደሚከለክል፣ መድኃኒቱን ማስተዳደር የጤና ፈቃድ ባለው ባለሙያ ሃኪም መረጋገጥ እንዳለበት፣ እና የሠራተኛ አባል የመድኃኒት አስተዳደር የተረጋገጠ ሥልጠና መርኃግብር የወሰዱ መሆን እንዳለባቸው ያስቀምጣል። ተጨማሪ መረጃ ምናልባትም በ DCMR 5ሀ § 153 ላይ ሊገኝ ይችላል።

በዋና እና በውኃ ላይ ጫወታ ጊዜ ለልጅ ዕድገት መሰረተ ልማት የሚያስፈሉጉ

በልጆቻችን እንክብካቤ ማድረግ አዋጅ , DCMR 5ሀ § 157 አስተየት እንደ ተሰጠው ለዋና እና ለወኃ ላይ ጫወታ ግዴታዎችን ያስቀምጣል። በተለያዩ በውኃ ላይ እንቅስቃሴ ጊዜ ለትክክለኛው ቁጥጥር የተለዩ ግዴታዎችን ሬሾው ግልጽ ተደርጓል። ፈቃድ ያለው ግለሰብ ልጆች በሚዋጁበት ወይም በውኃ ውስጥ በሚጫወቱበት ጊዜ፣ የሕጻናት መዋኛዎችን፣ በእግር ውስጥ የሚኬድ በት መዋኛ፣ እና ሙሉ በሙሉ ጥልቅ የሆነ መዋኛዎችን አካቶ፣ ፈቃዱ የተሰ ጠው ሰው የአዋቂ ሰዎች ቁጥር ከልጆቹ ጋር በሚመጥን መልኩ ማቅረባቸውን እና ከውኃ ደኅንነት ግድታዎች በ DCMR 5ሀ § 157 ላይ የተቀመጠውን ግድ ታዎች ጋር እንደሚሄድ ያረጋግጣል።

ፈቃድ ያላቸው የጦር መሣሪዎችን እና ተቀጣታይ ፈንጂውችን ማስቀመጥ - የልጅ ዕድገት ቤት እና የተስፋፋ ቤት

የDCMR 5ሀ §§ 167.7 እስከ 167.8 የልጅ ዕድገት የቤት ለቤት ፈቃድ ያለው ግለሰብ የተፈቀደለት ጠመንጃ፣ ሽጉጥ፣ ሳንጃዎችን ወይም ሌሎች ፈቃድ ያላቸውን የጦር መሳሪያዎችን እና ተቀጣጣይ ፈንጂዎችን የልጅ ዕድገት በሚሰጥበት ቤት ወይም በተስፋፋው ቤት ውስጥ አገልግሎት የሚያገኙ ልጆች እንደማይደርሱበት፣ እንዳልተጫነ፣ ተገቢ በሆነ ተስቦ በሚቆለፍ ዕቃ ውስጥ እንደሚያስቀምጥ፣ እና ደኅንነቱ በተጠበቀ ቦታ መቀመጡን፣ በሚቆለፍበት ጊዜ፣ ያለ ቁልፍ ሊከፈት እእንደማይችል፣ ውሂደት ወይም ሌሎች ያልተቆለፈ ማካኒዝም እና በዚያ ቦታ ላይ የሚገኙትን የጦር መሳሪያዎችን ወይም ተቀጣጣይ ፈንጂዎችን ሥልጣን የሌለው ሰዎች ከማግኘት እና በራሳቸው ከመያዛቸው መከልከል እንደሚችል ማረጋገጥ እንዳለበት ያስቀምጣል። ተቀጣጣይ ፈንጂዎች ደኅንነቱ በተጠበቀ የማከማቻ ቦታ ላይ መከማቸት አለባቸው። ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ በዚያ አገልግሎት የሚያገኙ ልጆች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ፈቃድ የተሰጣቸው ጠመንጃ፣ ሽጉጥ፣ ሳንጃ ወይም ሌሎች የጦር መሳሪያ እና ተቀጣጣይ ፈንጂ በልጅ ዕድገት ቤት ወይም በተስፋፋ ቤት ውስጥ መኖሩን ማስታወሻ ማቅረባቸውን መረጋገጥ አለባቸው።

ለደንበቹ ሙሉ ጽሑፍ እና ለተጨማሪ መረጃ፣ :
http://bit.ly/2krnteR ይጎብኙ

የአድራሻ መረጃ፡

የፈቃድ እና የአቤቱታ ክፍል
(202) 727-1839
osse.delcommunications@dc.gov

District of Columbia
Office of the State Superintendent of Education

810 First Street NE, Ninth Floor
Washington, DC 20002

osse.dc.gov
facebook.com/ossedc
@OSSEDC
(202) 727-6436